በደቡብ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት
የግብይትና ኅብረት ስራ ቢሮ
*South Nations, Nationalities and Peoples' Regional State*
**Marketing & Cooperative Bureau**

ቁጥር፡ ግ/ኅ/ሥ/ሹ-4/1/849/07
Rf/no
ቀን፡ 8/04/07

**ለኢፌዲሪ መንግስት የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**
**አዲስ አበባ፤**

**ጉዳዩ፡- ዉክልናን ይመለከታል፤**

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግስት በክልሉ የሚታየዉን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍ የፌዴራሉን መንግስት ፖሊስና ስትራቴጂ መነሻ በማድረግ ክልላዊ የቤት ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ አዘጋጅቷል፡፡

ፖሊሲዉንና ስትራቴጂዉን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ደንቦችንና መመሪያዎችን በማዉጣት ያጸደቀ ሲሆን ከነዚህ መመሪያዎች አንዱ በዉጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያንና ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን በመኖርያ ቤት ኅብረት ስራ ማህበር በመመዝገብና በማደራጀት በቤት ልማት ፕሮግራም ለማሳተፍ የወጣ መመሪያ ቁጥረ 08/2007" ነዉ፡፡

በዚሁ መመሪያ ለክልሉ ግብይትና ኅብረት ስራ ቢሮ በተሰጠዉ ተግባርና ኃላፊነት በሚለዉ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ቢሮዉ "በዉጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዉያንና ትዉልደ ኢትዮጵያዉያንን እና ተመላሽ ዲያስፖራ በመኖሪያ ቤት ኅብረት ስራ ማኅበር ተደራጅተዉ ለመመዝገብ እንደአስፈላጊነቱ ዉክልና በመስጠት እንዲደራጁ ያደርጋል፡፡ "በሚል ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም በመመሪያዉ መሠረት ቢሮዉ ለዉጭ ጉዳይ ሚኒስተር የማደራጀት ዉክልና የተሰጠ መሆኑንና ከዚሁ ደብዳቤ ጋር በቢሮዉ በኩል የተዘጋጀዉን መተዳደሪያ ደንብ/ሞዴል/ አንድ ጥራዝ እና አስፈላጊ ቅጻ ቅጾችን አባሪ አድርገን የላክን መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

SNNPRS Cooperative Marketing Bureau
NUREDIN MOHAMMED KEMAL
የቢሮ ኃላፊ
BUREAU HEAD

**እንዲያዉቁት፤**

- ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

**ግልባጭ፤**

- ለደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግስት ን/ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ
- ለመቤታችን የኅብረት ስራ ልማት ዋና ስራ ሂደት

**ሀዋሳ፤**

ም/ተ E-Mail smarketingand cooperative@yahoo.com
ስ.ቁ. 0462-20-20-16 Tel: 0462-20-88-35
ፋክስ 0462210041/0462207214 Fax:
ፖ.ሣ.ቁ 866 P.O.Box
ሀዋሳ,ኢትዮጵያ
HAWASSA,ETHIOPIA

# በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት

# በውጪ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ /ሞዴል/

የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ

ሀዋሳ ታህሳስ 2/ 2007

# በውጪ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

# የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

ተመሳሳይ ዓላማና ፍላጎት ያለን ሰዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ኅብረት በመፍጠር የጋራ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻችንን በጋራ ለማስወገድ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለምንመሰርተው የኅብረት ሥራ ማህበር አመቺ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

ኅብረት ሥራ ማህበሩ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ለአባላት ተገቢውን የመኖሪያ ቤት አገልግሎት መስጠትና ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ማድረግ በማስፈለጉ፣

በክልሉ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ውስጥ በግልጽ ያልተገለጹ ድንጋጌዎችን ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመቺ በሚሆን መልኩ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በግልፅ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ይህንን ዓላማ ለማሳካት የተቋቋመውን የ------------------------------------------መኖሪያ ቤት መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚተዳደርበትንና የሚመራበትን መተዳደሪያ ደንብ ማውጣት በማስፈለጉ፣

እኛ በ------------------------------------------------------------------------------------------የምንገኝ የ---------------------------------------- መኖሪያ ቤት መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 37 መሠረት የሚከተለውን አጽድቀን አውጥተናል፡፡

## አንቀጽ 1 ስለኅብረት ሥራ ማህበሩ መቋቋም

የኅብረት ሥራ ማህበሩ በኢፌዲሪ ኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 9 እና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/1999 አንቀጽ 14 መሠረት ተቋቋሞ (በፌዴራል አዋጅ )በአንቀጽ 11 እና (በክልል አዋጅ) አንቀጽ 17 ድንጋጌ መሠረት ይህ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስያሜ ፣ አድራሻ ፣አርማና የአርማ ትርጉም

### 2.1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ

የኅብረት ሥራ ማህበሩ የ.............................................. የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማህበር ኃላፊነቱ የተወሰነ፣

## 2.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻ ፣

1. ክልል---------------------------

.2. ዞን-----------------

3.ከተማ አስተዳደር---------------------------------

4 ክፍለ ከተማ ..........................

.5 ወረዳ..............................

6ቀበሌ አስተዳደር----------------------------------

7 የቦታው ልዩ መጠሪያ ..................

8 የቤት ቁጥር ........................

9 ስልክ ቁጥር ................

10 ፖ.ሣ.ቁ. ....................

## 2.3. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዓርማ

አርማው ዙሩሪያ በ-----------------------------------------የተከበበ ሆኖ ግራና ቀኝ ----------------ያለበት

መሀሉ ላይ ------------------------------- በግርጌ -------------------------------መደቡ ------------ነው

## 2.4. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ ዓርማ ትርጉም

1. ---------------------------------------------------------------------------------
2. ---------------------------------------------------------------------------
3. .------------------------------------------------------------------------------
4. --------------------------------------------------------------------------------
5. --------------------------------------------------------------------------------

## አንቀጽ 3. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ

1. "የኅብረት ሥራ ማህበር" ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸዉን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ድርጅት ነዉ
2. "የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር" ማለት ተመሳሳይ ወይም የተለያየ ገቢ ያላቸው ግለሰቦች በፈቃደኝነት ተሰባስበው ገንዘባቸውን ፣ ጉልበታቸውን ፣ ዕውቀታቸውን በማስተባበር ዴሞክራሲያዊ አመራርና ቁጥጥር በማድረግ የመኖሪያ ቤት ችግርን በጋራ ለመወጣት የሚያቋቁሙት ማኅበራዊ ድርጅት ማለት ነው።
3. “የኢትዮጵያ ዳያስፖራ” ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው፡፡
4. “ዲፕሎማቲክ ፓውች” ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚሲዮን ኦፊሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ነው፣
5. “ሚሲዮን” ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ነው፣

6. “ነባር የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር” ማለት በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ በዝግ ሂሳብ ገንዘብ ያስቀመጠ፣ በግብይትና ህብረት ስራ ቢሮ የምዝገባ ሠርቲፊኬት የተሰጠውና እስካሁን ድረስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ ያልተረከበ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፡
7. "አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር" ማለት በማህበር በመደራጀት ታውን ሃውስ እና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ ይህ የምዝገባ ማስፈጸሚያ “መመሪያ ቁጥር 08/2007” ጸድቆ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚደራጅ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ማለት ነው፡፡
8. “በግል ተመዝጋቢ” ማለት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአፓርትመንት ወይም በታውን ሃውስ በተናጠል ተመዝግቦ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ነው፡፡
9. "የውክልና ማስረጃ" ማለት በህግ የተደነገገ ሥርዓትን ተከትሎ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል /ውልና ማስረጃ - Notary Public/ ወይም ሚሲዮን በአካል ቀርቦ የተሰጠ፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውልና ማስረጃ መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ነው፡፡
10. "ዲፕሎማት" ማለት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች መንግታስዊ መሥሪያ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሚሲዮኖች በውጭ ግንኙነት መስክ ተመድቦ የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው፣
11. "ተመላሽ ዳያስፖራ" ማለት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ ከተመለሱ ከሁለት ዓመት በላይ የቆዩ እና በተለያዩ የሥራ መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው፡፡
12. “ታውን ሀውስ” ማለት ከጂ+0 እስከ ጂ+2 ወለል ያለው ራሱን የቻለ መጠነኛ ግቢ እና መግቢያ ያለው የመኖሪያ ህንፃ ሲሆን ከአጐራባች መኖሪያ ቤቶች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡
13. “አፖርትመንት” ማለት ጂ+3 እና ከዚያ በላይ ወለል ያላቸው በየከተሞቹ ደረጃ በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ሕንፃዎች ሆነው በጋራ የመኖሪያ ቤት ህግ መሠረት በግል ባለቤትነት የሚያዝ የተሟላ የመኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡
14. “ቢሮ” ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግሥት የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ነው፤
15. “ኢንተርፕራይዝ” ማለት በማህበራት የሚከናወኑ የመኖሪያ ቤት ግንባታዎችን ለማካሄድ ህጋዊ የግንባታ ስራ ፈቃድ ያለው በመንግስት የተቋቋመ የቤት ልማት ድርጅት ነው፡፡
16. "ግለሰብ" ማለት በሕግ መብት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው ማለት ሲሆን ይህም የወንድን ወይም የሴትን ጾታ የሚያካትት ነው::
17. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው::
18. "አባል" ማለት፡ የኀብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ እና በዚህ መተዳደሪያ ደብን በተደነገገዉ መሠረት የአባልነት መመዘኛዎችን አሟልቶ የተመዘገበ ማንኛዉም ግለሰብ ነዉ::
19. "የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ "ማለት የፌዴራል ኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 እና የዚህ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/1996 እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/1999 ማለት ነው::
20. "በሕግ ችሎታ የሌለው" ማለት ማንኛውንም ዓይነት የማሕበራዊ ኑሮውን ወይም ሕጋዊ ተግባር ለመፈጸም የማይችል ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት ያጣ ተቋም ማለት ነው::
21. "ጠቅላላ ጉባኤ "ማለት የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ አባላቱ የሚገኙበት ስብሰባ ነዉ::
22. "ልዩ ዉሳኔ"ማለት በኅብረት ሥራ ማኅበሩ አባላት ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረዉ ከአንድ ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት ዉስጥ በ2/3ኛ ( በሁለት ሦስተኛዉ) ድምፅ መፅደቅ ያለበት ዉሳኔ ነዉ::



የደቡብ/ብ/ብ/ ህ/ክ/መ/ግብይትና ኅብረት

23. "የሥራ አመራር ኮሚቴ " ማለት የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት እንዲመራ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጠን የተሰጠው አካል ነው፡፡
24. "አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ባለሥልጣን" ማለት ማንኛውም ዓይነት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት፣ ለመመዝገብ፣ ለመቆጣጠር፤ ለማስፋፋትና ቴክኒካዊ ድጋፍ ለመስጠት በሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው በክልል፣ በዞን፤ በልዩ ወረዳ፤ በወረዳና በከተማ መስተዳድር ደረጃ የሚገኝ የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ማለት ነው፡፡
25. ግዴታ፡ ማለት አንድ የኅብረት ሥራ ማኅበር አባል ከኅብረት ሥራ ማኅበሩ ጋር በሚኖረዉ ግንኙነት አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚደነገገዉ መሠረት የሚገደድበት ሥርዓት ነዉ፡፡
26. በዚህ መመሪያ ዉስጥ በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## አንቀጽ 4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማና ተግባር

### 4.1 ዓላማ

1. ያለባቸውን የመኖሪያ ቤት ችግር በጋራ ጥረት ለመፍታት ፍቃደኛ የሆኑና ፍላጎት ያላቸውን አባላት በማሰባሰብ በህብረት ሥራ ማህበራት መርህ መሠረት እንዲደራጁ ማስቻል፣
2. ፈቃደኛ የሆኑና ፍላጎት ያላቸው ዜጎች በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውን፣ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን በማቀናጀት የመጠለያ ችግሮቻቸውን በጋራ ጥረት ሊፈቱ የሚችሉበትን አማራጭ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
3. የኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተውና ገንዘብ ቆጥበው በጋራ ቤት በመገንባት የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት፣
4. የኅብረት ሥራ ንድፈ ሃሳብ ዓላማና ተግባር በአባላቶቹ አመለካከት ውስጥ ስርፆ እንዲገባና ወደ ተግባር እንዲለወጥ ማስቻል፣
5. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በጋራ ሕንፃ የመጠለያና የአካባቢ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ አርአያነት ያለው ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፣
6. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መካካል የመደጋገፍ ባህል እንዲያዳብሩ በማድረግ እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱና እንዲተጋገዙ ማስቻል፣
7. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በተናጠል ሊወጧቸው የማይቻላቸውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች በጋራ መፍታት፣
8. የመኖሪያ ቤት ህንፃው በተሰራበት አካባቢ ያልተሟሉ የመሠረተ ልማት አውታሮች እንዲቋቋሙና ምቹና ተስማሚ የመኖሪያ አካባቢ እንዲሆኑ ማድረግ፣
9. የአባላቱን መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችሉ የተለያዩ አገልግሎቶችን በማጥናት መተግበር፣
10. ከሌሎች አቻ ህብረት ሥራ ማህበራት ጋር ትብብር በመፍጠር ሁለተኛ ደረጃ የህብረት ሥራ ማህበራት ህብረት (ዩኒየን) ማቋቋም፣

### 4.2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ተግባር

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በህብረት ሥራ ማህበር በመደራጀት የግንባታ ቦታ በማስፈቀድ የመኖሪያ ቤት ችግሮቻቸውን እንዲያቃልሉ ማስቻል፣
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት የቤት ባለቤት ለመሆን የሚያስችላቸውን የገንዘብ አቅም እንዲፈጥሩ ማድረግ፣
3. ከክልሉ ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ እና አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በቅርበት መስራት፣
4. አባላት ያስገቧቸውንና የተረከቧቸውን የወልና የግል ድርሻዎች በአግባቡ መያዝና ማስተዳደር፣

5. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ደንቦች፣ መመሪያዎችና የጠቅላላ ጉባኤውን ውሣኔዎች በመቀበል በስራ መተርጎም
6. . የማህበሩን ገንዘብና ንብረት ህጋዊ በሆነ ስርዓት መያዝና ስራ ላይ ማዋል፣
7. የአባላትን መብትና ጥቅም ማስከበር፣
8. የመኖሪያ አካባቢን ማፅዳትና ማስዋብ፣
9. የመኖሪያ አካባቢን ፀጥታ ማስከበር ፤
10. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላትና ቅጥር ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣
11. የተሰሩት ህንፃዎች ለታቀደላቸው ዓላማ እንዲውሉ ማስቻል፣
12. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጽ/ቤት በሰው ሃይልና በመገልገያ ዕቃዎች የተሟላ ሆኖ ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል፣

## አንቀጽ 5. የኅብረት ሥራ መርሆዎችና እሴቶች

### 5.1 መርሆዎች

1. አባልነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተና ለሁሉም ክፍት መሆን
2. የአባላት ዲሞክራሲያዊ ተሣትፎ አሰራርና ቁጥጥር
3. የአባላት ኢኮኖሚያዊ ተሣትፎ
4. ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆንና ራስን በራስ ማስተዳደር፣
5. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለአባላት፣ ለማኅበሩ ለተመራጮችና ለቅጥር ሠራተኞች ትምህርት፣ ስልጠና መስጠትና አስፈላጊና ወቅታዊ መረጃ ለሚመለከተው አካል መስጠት፣
6. ከአቻ ኅብረት ሥራ ማኅበራት መካከል የእርስ በርስ ትብብር/መረዳዳት/ መኖር፣
7. ለህብረተሰብ ትኩረት መስጠትና ማህበራዊ ሃላፊነትን መወጣት

### 5.2 እሴቶች

### 5.2.1 የኅብረት ሥራ ማህበሩ እሴቶች

1. ራስን መቻል /መርዳት
2. የራስ ኃላፊነት/ የግል ሃላፊነት መወጣት
3. ዲሞክራሲ አሠራን ማስፈን
4. እኩልነትና ፍትሃዊነት ማስፈን
5. አንድነትና የጋራ መደጋፍ

### 5.2.2 የስነ-ምግባር ዕሴቶች

1. ማህበራዊ ሃላፊነትና ተጠያቂነት
2. መረዳዳት/ መተባበርና ስሌሎች ድጋ ማድረግ
3. ግልጸኝነት
4. ታማኝነት ናቸው

## አንቀጽ 6. የአባልነት መሥፈርት ና አደረጃጀት

### 6.1 የአባልነት መሥፈርት

በህብረት ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 111/99 አንቀጽ 19 መሰረት የአደረጃጀት መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል፡-

1. እድሜው ከ18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ በህግና በፍርድ ያልተከለከለና ፣ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ እና ትውልደ ኢትዮጵያዊ፣
2. በአካል መቅረብ የማይችል ከሆነ የታደሰ ፓስፖርት ፎቶ ኮፒና በፍ/ቤት ወይም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የተረጋጋጠ ውክልና ማቅረብ ይኖርበታል፣
3. በዚህ መመሪያ አባሪ ቅፅ ቁጥር 005 የተገለጸውን የቤት ፍላጎት ማመልከቻ ቅጽ በራሱ ወይም በተወካዩ አማካኝነት መፈረም ይኖርበታል፣
4. በአንድ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ውስጥ በውክልና ለማስፈጸም አንድ ተወካይ ለአንድ አባል ብቻ ውክልና መቅረብ ይኖርበታል፤
5. የቤቱን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ በምዝገባ ወቅት በዝግ ሂሳብ የሚያስቀምጥና እንዲሁም ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዝግ ሂሳብ ማስገባት የሚችል፣
6. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በክልሉም ሆነ በየትኛውም የሀገሪቱ ከተሞች የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤
7. የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ዓላማ መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎችን ለመፈጸም ፈቃደኛ የሆነ
8. በህግ ችሎታ ያለ ማንኛውም አባል መሆን ይችላል

### 6.2 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት አደረጃጀት

6. 2.1 አባላቱ የሚደራጁት በኤምባሲያቸው አማካኝነት ይሆናል፡፡ በመመሪያ ቁጥር 08/2007 ቤቶች ደረጃ መሰረት በመኖሪ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ የአባላት ቁጥር ዝቅተኛው 10 እና ከፍተኛው 24 ሆነው ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

ሀ) **በመሪ ከተማ-** በአፓርትመንት (G+4 እና በላይ) መኖሪ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ የአባላት ብዛት12 (አዲስም ሆነ ነባር) ፣
ለ) **በከፍተኛ ከተሞች-** በአፓርትመንት (G+3 እና በላይ) መኖሪ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ የአባላት ብዛት 10(አዲስም ሆነ ነባር) ፣
ሐ) **በመካከለኛ ከተማ አስተዳደር ከተሞች-** በታውን ሃውስ (G+2) መኖሪ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ የአባላት ብዛት10 (አዲስም ሆነ ነባር) ይሆናል፡፡
መ/ሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የአባላት ብዛት ጎደሎ ቁጥር መሆን የለበትም፣

6.2.2 የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አስፈላጊውን የአደረጃጀት ሰነዶች የሚያቀርብ ይሆናል፡-

- የማመልከቻ ቅጽ፣
- ሞዴል መተዳሪያ ደንብ፣
- የአባላት ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ፣
- የተወካዮች ዝርዝር መረጃ ሠንጠረዥ፣
- የምስረታ ቃለ ጉባዔ ላይ ውይይት የሚደረግባቸውና ውሣኔ ማግኘት የሚገባው ነጥቦች፣

6.2.3 የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከተደራጀ በኋላ በኤምባሲው በኩል ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚላኩ ሰነዶች፣

6.2.3.1. 3 ቅጂ መተዳደሪያ ደንብ በተመረጡ ሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የተፈረመና የመስራች አባላት ዝርዝር፣ አድራሻና ፊርማ፣ የውሣኔ ስምምነት በስተጀርባው የተያያዘ፣

6.2.3.2 የውክልና ማስረጃ ፎቶ ኮፒ /በሁለት ቅጂ/ ለአንድ አባል አንድ ተወካይ፣

6.2.3.4 የምስረታ ቃለ ጉባዔ ይኸውም፡-

- የኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የፀደቀበት፣
- የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓርማና ማህተም የተወሰነበት፣
- የሥራ አመራር ኮሚቴና የቁጥጥር ኮሚቴ የተመረጡበት የአባላት ዝርዝርመረጃ፣
- የተወካዮች ዝርዝር መረጃ ያካተተ ሆኖ በሁለት ኦርጂናል ቅጽ ተዘጋጅቶ በተመሣሣይ ሁኔታ ይቀርባል፡፡

6.3 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም የተላከለትን ሰነድ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተሙን በማሳረፍና በማረጋገጥ ማህበሩ ለመረጠው ለደቡብ ክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ በመሸኛ ደብዳቤ ይልካል፡፡

6.4 የደቡብ ክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ በተላከለት ሰነድ መሠረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት ተወካዮችን በመቀበል የራሳቸውን የሥራ አመራርና የቁጥጥር ኮሚቴ እንዲመርጡ ያደርጋል፡፡ የሥራ አመራ ኮሚቴው ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር፣ ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ ይኖሩታል፡፡ ሂሳቡንም በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳሉ፡፡

6.5 የደቡብ ክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም በተከፈተ ዝግ የቁጠባ ሂሳብ አባላቱ በየስማቸው የመኖሪያ ቤቱን የግንባታ ክፍያ 50 ፐርሰንት ያሟሉና ሌሎች ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

6.7 የኅብረት ሥራ ማህበሩ የግንባታዉን ወጪ 50% እዲከፍል የምዝገባ ምሥክር ወረቀት ከ2 ቅጂ የመተዳደሪያ ደንብ እና 1 ቅጂ የምሥረታ ቃለጉባኤ ጋር በመስጠት የራስጌና የግርጌ ማህተም በተወካዮቹ አማካኝነት እንዲያስቀርጽ ይደረጋል፡፡

6.8. በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስምና አድራሻ መሠረታዊ የሂሳብ ሰነዶችንና መዛግብቶችን በሚሟላት ህጋዊ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን በመዘርጋት የሂሳብ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡

6.9 የክልሉ ቢሮ የተመዘገቡና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ለቤቶች ልማትና አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም ጽ/ቤት በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል፡፡

6.10. የኅብረት ሥራ ማህበሩ አድራሻና የሥራ ቦታ ማህበሩ በሚረከበው የግንባታ ቦታ ላይ ይሆናል፡፡

## 7. በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮኖጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በታውን ሀውስ እና አፓርትመንት ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸው የሚከተሉትን በማሟላት ምዝገባ ማከናወን ይችላሉ፡፡

1. የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና የሚኖሩበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
2. የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆኑ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣



ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ

3. ያገባ/ች ከሆነ የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጅውን፣
4. ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶ ግራፍ፣
5. ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. ተመዝጋቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣
7. በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ሙሉ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣
8. በመረጡት የቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት በሚኖሩበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጡና መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በውጭ ምንዛሪ ለመክፈል ፈቃደኛ የሆኑና በአገር ውስጥ በሚከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣
9. ግለሰቡ እንደተደራጀ የሚቆጠረው የግንባታውን ወጪ 50 ፐርሰንት ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣
10. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በክልሉም ሆነ በየትኛውም የሀገሪቱ ከተሞች የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ ሊሆን ይገባል፡፡

## 8 በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች

በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር ለመደራጀት የሚፈልጉ ማህበራት አባላት ፡-

1. ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በክልሉም ሆነ በየትኛውም የሀገሪቱ ከተሞች የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
2. በመንግስት በተዘረጉት ሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች ላይ ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግቦም ከሆነ ምዝገባውን መሠረዙን ወይም መተውን ግዴታ መግባት የሚችል፣
3. አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ የሚችለው እና እንደተመሠረተ የሚቆጠረው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ መክፈል ሲችሉ ብቻ ነው፣
4. የቦታውን የሊዝ መነሻ ዋጋ ለመክፈል የሚችል፣
5. የነባር ማህበራትን አመዘጋገብ በተመለከተ የክልሉ ግብይትና ህብረት ስራ ቢሮ ከክልሉ ንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ተስማምተው በሚያቀርቡት ዝርዝር ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣
6. ሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው መጠሪያ ስያሜ ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን በማህበሩ ስር ያሉ አባላት በሙሉ የሚቀርብላቸውን ቅጽ 005 በራሳቸው ካልቻሉም በወኪላቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ መሙላት ይገባቸዋል፣
7. የህብረት ስራ ማህበር አባላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣
8. የሚደራጁ ማህበራት የራሳቸውን የግንባታ ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ዲዛይኑ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፣
9. በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በክልሉ

የመረጡትን ከተማ ለይተው እንዲያሳውቁና አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፣

## አንቀጽ 9. ስለ ስብሰባና ድምፅ አሰጣጥ

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምፅ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል ያለው የዕጣ መጠን ግምት ውስጥ ሳይገባ በስብሰባ ላይ ተገኝቶ የሚሰጠው ድምፅ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ በድምፅ ብልጫ የሚወሰን ይሆናል፡፡
4. የድምፅ አሰጣጡ ስነስርዓት ግልፅ በሆነና በማያሻማ መልኩ እጅን በማውጣት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
5. ተወካዮች አባሉን ተክተዉ ድምፅ የመስጠት መብት የላቸዉም፡፡

## አንቀጽ 10. ስለምርጫ ስነስርዓት

1. ማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል የሚመረጠው በጠቅላላ ጉባዔ ምርጫ ይሆናል፡፡
2. የምርጫው ስነስርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው በአስመራጭ ኮሚቴ ይሆናል፡፡
3. የአስመራጭ ኮሚቴው በዕለቱ በመስራች ኮሚቴው ወይም የቀድሞው የሥራ አመራር ቦርድ አማካኝነት እንዲመረጥ ይደረጋል፡፡
4. የምርጫ ስነ-ስርዓቱ በሚፈፀምበት ወቅት እንደአስፈላጊነቱ የሚሲዮኑ ተወካይ መገኘት ይኖርበታል፡፡
5. አስመራጭ ኮሚቴው በጥቆማ የቀረቡለትን እጩዎች አብላጫ ድምጽ ያግኙትን ያስመርጣል፡፡
6. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን በዕጩነት በመጠቀም ማቅረብ አይችሉም፡፡ ሆኖም ጉባዔው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት ለውድድር ሊያቀርባቸው ይችላል፡፡
7. አስመራጭ ኮሚቴው በቀድሞዎቹና በአዲሶቹ ተመራጮች መካከል ርክክብ እንዲፈፀም የማድረግ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡
8. አዲሶቹ የኮሚቴ አባላት ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው የተጣለባቸውን ሃላፊነት መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 11 . ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባልነት ለመመረጥ ስለሚያበቁ መስፈርቶች

1. በስነምግባር ጉድለት ተከሶ ያልተፈረደበት፣
2. ጥሩ ስምና ስነምግባር ያለው፣
3. የአመራር ችሎታ ያለው፣
4. እድሜው ከ25 ዓመት በላይ የሆነ፣
5. ለኅብረት ሥራ ማህበሩ እድገትና ጥንካሬ ተቆርቋሪ የሆነ፣
6. በኅብረት ሥራ ማህበራት መርሆዎችና እሴቶች ጽኑ እምነት ያለው፣
7. የማህበሩ ቅጥር ሠራተኛ ያልሆነ፣
8. ከሌሎች ጋር ተባብሮና ተመካክሮ ለመስራት ፍላጎት ያለውና የሚችል፣
9. ማህበሩ ከሚያከናወናቸው ማናቸውም ሥራዎች ጋር በጥቅም የሚያገናኝ ተግባር የማይሰራ፣

## አንቀጽ 12 . የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር አካላት

1. ጠቅላላ ጉባዔ፣
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ፣
3. የቁጥጥር ኮሚቴ፣
4. የቴክኒክና የማህበራዊ ጉዳይ ኮሚቴ፣
5. ሌሎች ኮሚቴዎች፣

## አንቀጽ 13 . የኅብረት ሥራ ማህበሩ የጠቅላላ ጉባኤ

### 13.1 የጠቅላላ ጉባኤ አቋም

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ እያንዳንዱ አባል በአካል የሚገኝበት ስብሰባ ነው፡፡
2. ጠቅላላ ጉባዔው በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ ሰጪ ነው፡፡

### አንቀጽ 13.2 ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት

### 13.2.1 መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

1. የኅብረት ሥራ ማኅበሩ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይደረጋል፣
2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው በአጀንዳው መሠረት ሊነጋገር የሚችለው ምልዓተ ጉባኤ ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ ሲገኙ ይሆናል፡
3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤው ካልተሟላ በ15 ቀናት ውስጥ ሁለተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የተጠራው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙት አባላት መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ይካሄደል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ምልዓተ ጉባኤው ሳይሟላ የተካሄደው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፋቸው ዉሳኔዎች ሁሉም አባላት በተገኙበት እንደተላለፈ ይቆጠራል ፡፡ ውሳኔውም ባልተገኙት የጉባኤ አባላት ላይም ተግባራዊ ይሆናል ፡፡

### 13.2.2 አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

1. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው 2/3ኛው የተገኙበት ነው
2. የማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ከጠቅላላ አባላቱ መካከል 1/3ኛው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ሲጠይቁ የ15 ቀን ቅድሚያ ማስተወቂያ በማውጣት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በ15 ቀን ውስጥ ድጋሚ ( ሁለተኛ ጊዜ) ጥሪ ይተለለፋል ፣ ጥሪው ስለመድረሱ አባላት በፊርማቸው እንዲያረጋግጡ ይደረጋል፡፡
4. ለሁለተኛ ጊዜ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ተጣርቶ ምልዓተ ጉባኤ ባይሟላ ለሦስተኛ ጊዜ በ10 ቀናት ውስጥ ይጠራል ፡፡
5. ለሦስተኛ ጊዜ በተጠራ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙት የጉባኤ አባላት ጉባኤው ይካሄዳል ፡፡ ውሳኔው በዕለቱ ባልተገኙ የጉባኤ አባላት ላይም ተግባራዊ ይሆናል ፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ላይ በተገለፀው ሁኔታ ተፈፃሚነት ሳያገኝ ሲቀር አግባብ ያለው ባለሥልጠን በኅብረት ሥራ አዋጅና አግባብነት ባለቸው አዋጆች መሠረት ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል ፡፡

7. ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውስጥ 2/3ኛው/ ሁለት ሦስተኛው/ ሲገኙ ምልአቴ ጉባኤ ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ የሥራ አመራር ኮሚቴ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጠን ጥሪውን ያደርጋል፡፡ ይኸውም ጠቅላላ ጉባኤው በሥራ አመራር ኮሚቴ እንደተጠራ ይቆጣራል ፡፡
9. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ህልዉና ጋር የተያያዙ ማለትም መፍረስ፣ መከፈል፣ መዋሃድ፣ ደንብ ማሻሻል፣ ወይም መቀየር ... ወዘተ የመሳሉትን መወሰን የሚቻለው ከጠቅላላ አባላት 2/3-ኛው በስብሰባው ከተገኙ በሙሉ ድምጽ ሲወስን ብቻ ነው፡፡

## 13.2 የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፡፡
2. 2 የኅብረት ሥራ ማህበሩን ህገ ደንብና መመሪያ ያፀድቃል፡፡
3. የኅብረትሥራማህበሩን የስራ ማስኬጃ ግንባታዉን ክፍያዎችን ይወስናል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዕቅድና በጀት ያፀድቃል፡፡
5. 5 ዓመታዊ የስራ ሪፖርት የምርመራ ውጤት ገምግሞ ይወስናል፡፡
6. የማህበሩን የኦዲት ሪፖርት በመገምገም ያፀድቃል፡፡
7. ሕብረት ሥራ ማህበሩ ከሌሎች አቻ የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ለመዋሃድ ከፈለገ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡
8. የቤቶች ድልድልን፣ ጥገናና እድሣት ያፀድቃል፡፡
9. ሌሎች ከሥራ አመራር ኮሚቴው አቅም በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ይወስናል፡፡

# አንቀጽ 14 . የሥራ አመራር ኮሚቴ

## 14.1 አቋም

1. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል፡፡
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሐፊ፣ ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ የሚኖሩት ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱና እንደስራው ስፋትና ጥልቀት ም/ሂሳብ ሹምና አባላት በተጨማሪ ሊኖሩት የሚችል ይሆናል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ከ 5 በታች ሊሆን አይችልም፡፡
4. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን 3 ዓመት ይሆናል፡፡
5. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፡፡ በተመረጡበት የሥራ ዘመን ውስጥ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሩ ይችላሉ፡፡
6. የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜና ቦታ ሊደረግ የሚችል ሲሆን ቢያንስ በሩብ ዓመት ውስጥ አንድ ጊዜ መደረግ ይኖርበታል፡፡
7. የሥራ አመራር ኮሚቴ በአብላጫ ድምፅ ይወስናል፡፡
8. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ከተሰጣቸው ተግባርና ሃላፊነት ውጪ መስራት አይችሉም፡፡
9. የሥራ አመራር ኮሚቴ የሥራ ዘመኑን ሲያጠናቅቅ በዘመኑ ያከናወነውን ተግባር የማስመርመርና ለአባላቱ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፡፡
10. የሥራ አመራር ኮሚቴ የአገልግሎት ዘመኑ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚያስተላልፈው ውሣኔና የሚሰጠው አገልግሎት ህጋዊነት አይኖረውም፡፡

11. የሥራ አመራር ኮሚቴ የምርጫ ለውጥ በተደረገ በአንድ ወር ውስጥ ለተተኪው ኮሚቴ ስራውን ማስረከብ ይኖርበታል፡፡
12. የሥራ አመራር ኮሚቴ የሥራ ዘመን አጠናቆ ሲሰናበት በዘመኑ ያከናወነውን ተግባር የማስመርመርና ለአባላቱ የማሳወቅ ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡
13. የሥራ አመራር ኮሚቴ የስራ ሽግሽግና ዝውውር አድርጎ መስራት ይችላል፡ቢሆንም የተጓደሉ አባላትን ሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አስመርጦ ማሟላት ይኖርበታል፡፡
14. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በተለያየ ምክንያት ቢጓደሉ ቀሪዎቹ ተመራጮች ከግማሽ ወይም ከዚያ በታች በሆነ ቁጥር አገልግሎት መስጠት አይችሉም፡፡
15. የሥራ አመራር ኮሚቴ በማንኛውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባዔው ውሣኔ በከፊልም ሆነ በሙሉ ሊብተን ይችላል

## 14.2 ሥራ አመራር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1. የጠቅላላ ጉባዔውን ውሣኔ ያስፈፅማል
2. የኀብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ አዘጋጅቶ ወይም አሻሽሎ ለጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔ ያቀርባል፡፡ ከፀደቀም በኂላ አግባብ ባለው ባለሥልጣን እንዲመዘገብና ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
3. የኀብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ይሰበስባል በአግባቡ ሥራ ላይ ያውላል፤
4. የኀብረት ሥራ ማህበሩን ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ በጉባዔውም ሲፈቀድለትም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
5. የኀብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ መዝገብ ያቋቁማል በአግባቡ፤ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡
6. ኀብረት ሥራ ማህበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ኦዲት እንዲደርግ ምቹሁኔታዎችን ይፈጥራል፤
7. የኀብረት ሥራ ማህበሩ የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡
8. ከኀ/ሥራ ማህበሩ ለመሰናበት የሚፈልጉ አባላትን ማመልከቻ ተቀብሎ ይስተናገዳል፡፡
9. ለማኛውም ህጋዊ ጉዳይ የኀብረት ሥራ ማህበሩ ተጠሪና ተወካይ ሆኖ ያገለግላል፡፡
10. የኀብረት ሥራ ማህበሩን የጋራ ህንፃ ግንባታ ይከታተላል ሲጠናቀቅም በአግባቡ ይይዛል ያስተዳድራል፡፡
11. የኀብረት ሥራ መርሆዎችና እሴቶች በአባሉ መካከል ሰርፀው እንዲገቡና በስራ እንዲተረጎሙ ያደርጋል፡፡
12. የኀብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ ምክር ቤቱን በመጥራትና በማወያየት ውሳኔ እዲስጥበት ያደርጋል ፡፡
13. የኀብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በሃላፊነት ይመራል፡፡
14. የአገልግሎት ዘመኑ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ጉባዔው የሚጠራበትንና ምርጫው የሚከናወንበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
15. እደአስፈላጊነቱ በጉባዔው ውሣኔና ወይም በማህበሩ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፡፡

## አንቀጽ 15 .የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ሥልጣንና ተግባር

### 15.1 የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ

1. የጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አመራር ኮሚቴን ስብሰባዎች በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡
2. የኀብረት ሥራ ማህበሩን በመወከል በማንኛውም ቦታ ይገኛል፡፡ይከሳል ፣ይከሰሳል፣ውል ይዋዋላል፡፡
3. ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡
4. በኀብረት ሥራ ማህበሩ ስም በሚተላለፉ ደብዳቤዎችና ሰነዶች ላይ ይፈርማል፡፡

5. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ያንቀሳቅሳል፡፡
6. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ጋር በቅርበት ይሰራል፣ የሥራ እንቅስቃሴውን ይከታተላል፡፡
7. የኅብረት ሥራ ማህበሩን እንቅስቃሴ አስመልክቶ አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡
8. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የመተዳደሪያና ውስጠ ደንብ በሥራ እንዲተረጎም ያደርጋል፡፡
9. የኅብረት ሥራ ማህበሩሀብት በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

## 15.2 ምክትል ሰብሳቢ

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የቅርብ ረዳት ሆኖ ይሰራል፡፡
2. ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ በማይኖርበት ወቅት ወይም መስራት በማይችለበት ጊዜ እርሱ ተተክቶ ይሰራል፣ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ ከሂሳብ ሹሙና ከገንዘብ ያዡ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ከሥራ አስኪያጅ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
4. ከሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢና ከፀሃፊው ጋር በመሆን የስብሰባ አጀንዳዎችን ይቀርፃል፡፡
5. ሌሎች በኮሚቴው የሚሰጡትን ተግባራት ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

## 15.3 ፀሐፊ

1. ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሰነድና ማህተም በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የስብሰባ ቃለጉባዔ ይይዛል፣ በፊርማ እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡
4. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጽህፈት ቤት ጋር በመሆን የጽሁፍና የደብዳቤ ልውውጥ ሥራ ያካሂዳል፡፡
5. ፀሀፊው በማንኛውም መልኩ በወጪ ደብዳቤ ላይ አይፈርምም
6. ከሥራ አመራር ኮሚቴው ሰብሳቢና ከምክትል ሰብሳቢው ጋር በመምከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፡፡
7. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢውና ምክትል ሰብሳቢው በማይኖርበት ወቅት ጊዜያዊ ሰብሳቢ በማስመረጥ ስብሰባውን ያካሂዳል፡፡

## 15.4 ሂሳብ ሹም

1. ኅብረት ሥራ ማህበሩ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ የሂሳብ መዛግብቶችና ሰነዶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ እንቅስቃሴ መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴን መሠረት በማድረግ ሥርዓት ባለው መልኩ እንዲሄድ ያደርጋል፡፡
3. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ከገንዘብ ያዥና ሰብሳቢ ጋር በመምከር የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ በስርዓት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የገንዘብ ገቢና ወጪ በትክክል ይመዘግባል ፤በወቅቱም መወራረዳቸውን ያረጋግጣል፡፡
5. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሰብሳቢእና ወይም ምክትል ሰብሳቢእና ከገንዘብ ያዥጋር የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
6. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ ሪፖርት እንዲዘጋጅና ለስራ አመራሪ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
7. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ እንዲመረመር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡
8. ሌሎች በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. እዳስፈላጊነቱከ ማህበሩ የስራ ስፋት አንፃር ሂሳብ ሹሙን የሚረዳ ሂሣብ ሠራተኛ ለቀጥር ይችላል፡፡

## 15.5 ገንዘብ ያዥ

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገቢና ወጪና በማስረጃ ተደግፎ ሲቀርብና በማህበሩ ሂሳብ ሹምና ሰብሳቢው ወይም ምክትል ሰብሳቢው ጣምራ ፊርማ ሲረጋገጥ ክፊያ ይከፍላል፡፡
2. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ ወደ ባንክ ያስገባል ከባንክ ወጪ ያደርጋል፡፡
3. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ በጥንቃቄ ይይዛል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ወጪና ገቢ በእለት ገቢና ወጪ መመዝገቢያ ባህርመዝግብ ላይ ይመዘግባል

## አንቀጽ 16 የቁጥጥር ኮሚቴ

## 16.1 አቋም

1. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ብዛት ከሦስት የማያንስ ሆኖ በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጡ ይሆናል፡፡
2. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ነው፡፡
3. ኮሚቴው ሰብሳቢ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖሩታል፡፡
4. የኮሚቴው የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ ከሁለት ተከታታይ የምርጫ ዘመን በላይ ማገልገል አይችልም ፡፡
5. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በሥራ አመራር ምክር ቤት /ቨንን/ በአባልነት ይሳተፈሉ፡፡
6. የቁጥጥር ኮሚቴው አባላት እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ያለ ድምፅ በታዛቢነት ተሣታፊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
7. የቁጥጥር ኮሚቴ ተመራጭ አባላት አገልግሎታቸውን አጠናቀዉ ከተሰናበቱ ከሁለት ተከታታይ የምርጫ ዘመን በኋላ የአባላቱ ቁጥር አነስተኛ ሆኖ ከተገኘ ለሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተመራጭ ለመሆን እንደገና መወዳደር ይችላሉ፡፡
8. ኮሚቴው በማንኛውም ወቅት በጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ ሊበተን ይችላል፡፡

## 16.2 ሥልጣንና ተግባር

1. የቁጥጥር ኮሚቴ ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሰነዶች ጠይቆ የማግኘት፣ የማየት፣ የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡
2. የጠቅላላ ጉባዔውን ውሣኔዎችና ህገ ደንቦች በትክክል በተግባር መተርጎማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
3. የሥራ አመራረ ኮሚቴ ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ እንደአስፈላጊነቱ የቁጥጥር ኮሚቴው የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ መጥራት ይቻላል፡፡
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ ስለመያዙና ሥራ ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡
5. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ በትክክል ሃላፊነቱን መወጣቱን ይከታተላል፡፡
6. የኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ በየዓመቱ ለጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል፡፡
7. የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በጊዜ ገደባቸው አስመርጠው ሥራቸውን ለተተኪዎች እንዲያስረክቡ የማድረግ ሃላፊነት አለበት፡፡
8. ሌሎች በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡት ተግባራት ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ17. ስለ ክርክር አወሳሰን

በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚነሱ ክርክሮች በኅብረት ሥራ ማህበራት መቋቋሚያ አዋጅ መሠረት በእርቅ መታየት ይኖርበታል፡፡ በእርቅና በስምምነት ሊፈቱ ያልቻሉ ጉዳዮች በአዋጅ ድንጋጌ መሠረት በሽምግልና ዳኝነት እንዲታዩ ይደረጋል፡፡

አንቀጽ 19 የጽ/ቤት አደረጃጀት

19.1 አቋም

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ቋሚ ጽ/ቤት ይኖረዋል፡፡
2. አዳስፈላጊነቱ ጽ/ቤቱ ቅጥር ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 20. የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሕጋዊ ሰውነትና የሃላፊነት ደረጃ

1. ኅብረት ሥራ ማኀበሩ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አዋጅና ደንብን መሰረት ማንኛውንም የሚፈለግበትን ፎርማሊቲ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ በክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ተመዝግቦ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2. ኅብረት ሥራ ማኀበሩ ሕጋዊ ሰውነት ካገኘ ለመክሰስ፣ ለመከሰስ ውል ለመዋዋልናሌሎች ተግባሮችን ለመፈጸም ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡
4. በኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ኃላፊነቱ የተወሰነ ነው

21. የአባላት መብትና ግዴታ

21.1 የአባላት መብት

1. ማንኛውም አባል የመምረጥና የመመረጥ፣
2. በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስብሰባ የመካፈልና ድምፅ የመስጠት እንዲሁም ማህበሩ የሚሰጠውን አገልግሎት የመጠቀም፣
3. ከአባልነት በፍቃዱ የመሰናበት፣ ከሥራ አመራር ኮሚቴ መልቀቂያ ደብዳቤ የማግኘት፣
4. በስሙ የተመዘገበውን የመኖሪያ ቤት ማከራየት፣ መሸጥ፣ መለወጥ፣ መስጠት፣ ማውረስ ወዘተ ይችላል፡፡
5. ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የፈለገውን መረጃ የማወቅና የማግኘት መብቶች ይኖሩታል፡፡

21.2 የአባላት ግዴታ

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብን መሠረት አድርገው የሚወጡ መመሪያዎችን ማክበርና ተግባራዊ ማድረግ
2. በማህበሩ ስብሰባ ላይ በመገኘት በውይይትና በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ተሣታፊ መሆን፣
3. የአብላጫውን ድምፀ ውሣኔ መቀበልና ተግባራዊ ማድረግ፤
4. የኅብረት ሥራ ማህበሩን የወል ንብረት መጠበቅና መንከባከብ፤
5. በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚፈለግበትን ክፍያ በወቅቱ መክፈል፣
6. በተረከበው የመኖሪ ቤት ውስጥ ሌሎችን ነዋሪዎች ላይ ተፅእኖ ሊፈጥር የሚችል ተግባር አለመፈፀም፣
7. በችሎታው ለማህበሩ አስተዋፅኦ ማድረግ፤
8. የህብረት ሥራ ማህበሩን እሴቶችናመርሆች መቀበልና መተግበር፤

9. በኮሚቴ አባልነት ሲመረጥ ማገልገል፤
10. ማንኛዉም የመኖሪያ ቤት ህብርት ስራ ማህበሩ አባል በመረጠዉ ቤት ዲዛይን አማካኝነት የቤቱ ወጪ 50% ለቤት ግንባታ ወጭ ቅድሚያ ክፍያ በምዝግባ ወቅት 50% ደግሞ ማህበሩ መሬት ስረከብ በወጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ማድርግ አለበት፡፡

## አንቀጽ 22 ከአባልነት ስለመሰናበት (ስለመሠረዝ)

### 22.1 በፈቃደኝነት

1. ማንኛውም አባል ከኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት በፈቃዱ መሰናበት ይችላል፡፡
2. ማንኛውም አባል ከአባልነት ለመሰናበት ሲፈልግ ጥያቄውን በጽሁፍ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የሥራ አመራር ኮሚቴ ጥያቄው በቀረበለት 15 ቀናት ባለሞላ ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡
4. ከመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት የሚሰናበት አባል ጥቅምና ድርሻው ይከበርለታል፡፡
5. ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር አባሉ በተሰናበተ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጥቅምና ድርሻውን ማግኘት ይኖርበታል፡፡

### 22.2 በአስገዳጅ ሁኔታ

1. ማንኛውም አባል የማህበሩን፤ ደንብና መመሪ የሚፃረር ተግባር ሲፈፅም ከተገኘ ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ በጠቅላላ ጉባዔው ውሣኔ መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡
2. አንድ አባል ለመኖሪቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ የገባውን ግዴታ መወጣት ካልቻለ ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡
3. ከመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በማህበሩ በሚቀመጠው ውስጠ ደንብ መሠረት ወራት ያህል ምንም ዓይነት ግንኙነት ሳያደርግ ከቀረ ከአባልነት እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡
4. አባሉበመኖሪያቤት ህብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ ያለውን ድርሻ ከግንባታ በፊት ወጪ አድርጎ ከወሰደ ከአባልነት እንደተሰናበተ ተደርጎ በምትኩ ሌላ አመልካች እንዲገባ ይደረጋል፡፡
5. አንድ አባል መሞቱ ሲረጋገጥ አባልነቱ ይቋረጣል፡፡

## 23 የአገልግሎት ክፍያ /መዋጮ/ና መመዝገቢያ

### 23.1 የአገልግሎት ክፍያ /መዋጮ/

1. የመኖሪያቤትኅብረት ሥራ ማህበሩ ለሚሰጠው አገልግሎት ከአባሉ መዋጮ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል የገንዘቡ መጠን ብር ------------------------------------------ ይሆናል ፡፡
2. የጋራ ሕፃው ጥበቃ እድሣት ጥገና ወዘተ የጋራ አገልግሎቶች ሲሆኑ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ተጨማሪ ገቢ እስከሌለው ድረስ በአባላቱ መዋጮ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡

3. የአገልግሎት ክፍያው መጠን እንደ ህንፃው የሥራ ስፋት በጠቅላላ ጉባዔ የሚወሰን ሲሆን፣ በወር ወይም በዓመት ተሰልቶ ሊቀርብ ይችላል፡፡
4. የአገልግሎት ክፍያው የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ካሉት አባላቱ የሚሰበስብ መዋጮ የሚቋረጥ ይሆናል፡፡

### 23.2. የመመዝገቢያ ክፍያ

1. ማንኛውም ግለሰብ አባል እንዲሆን ሲፈቀድለት የመመዝገቢያ ................ ብር ይከፍላል፡፡ ሕጋዊ የአባልነት ካርድ ይሰጠዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተከፈለው ገንዘብ አባሉ ከማኅበሩ ሲሰናበት ተመላሽ አይሆንም፡፡
3. የመመዝገቢያ ገንዘብ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ ማህተም ለማስቀረጽ፣መዛግብትና ሰነዶች መግዣ ይሆናል፡፡

### 23.3 ሌሎች የገቢ ምንጮች

ብድር፣ ወለድ ... ወዘተ የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ተጨማሪ ገቢዎች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 24 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ልዩ ልዩ መዛግብት

የመኖሪ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ፣

1. የአባላት መዝገብ፣
2. የቃለ ጉባዔ መዝገብ፣
3. የንብረት መዝገብ፣
4. የገቢ ደረሰኝ፣
5. የወጪ ማዘዣ፣
6. የገቢ መዝገብ፣
7. የወጪ መዝገብ፣
8. አጠቃላይ የሂሳብ ቋት፣
9. ሌሎች አግባብያላቸዉ ሰነዶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 25. ደመወዝ፣ አበልና የትርፍ ሰዓት ክፍያ

1. የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለቅጥር ሠራተኞች ደመወዝ፣ አበልና የትርፍ ሠዓት ክፍያ ይፈጽማል፡፡
2. የኮሚቴ አባላት ለተመረጡበት የሥራ ሃላፊነት ደመወዝ አይከፈላቸውም፡፡
3. የኮሚቴ አባላት ከተመረጡበት ተግባርና ሃላፊነት ጋር በተያያዘ በመንግስት አካላት በተደረገ ጥሪ የሚሰጥ ስልጠና፣ወርክሾፒ.ወዘተ ካለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ በአበል መልክ ክፍያ መፈጸም ይችላል፡፡

4. የአበል ክፍያው አፈፃፀም በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጠ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፡፡

5. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩ የቅጥር ሠራተኞች ካሉት የትርፍ ሰአት ክፍያ የማይከፍል ከሆነ በስራ ቀናት በሰራዉ ልክ ትርፍ በሠራበት መጥን እረፍት ይሠጠዋል፡፡

## አንቀጽ 26 ወራሽ ነት ስለመሰየም

1. አንድ አባል መሞቱ ሲረጋገጥ አባልነቱ ይቀራል፣
2. እያንዳንዱ አባል የሞት አደጋን በማሰብ ከማህበሩ ውስጥ ላለው ጥቅም ወራሽ መሰየም አለበት፡፡
3. ይህ ባልተደረገበት ሁኔታ በማናቸውም አጋጣሚ አባሉ ቢሞት በፍርድ ቤት የተወሰነለት ሰው ወራሽ ይሆናል፣
4. ከአባልነት የሚገኝ ጥቅም እንጂ አባልነት አይወረስም፣ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ወራሹን ብቁ ሆኖ ካገኘው በአባልነት ሊቀበለው ይችላል፣

## ኣንቀጽ 27 የህንፃው አጠቃቀምና አስተዳደር

ህንፃው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኂላ እንደ አባላቱ ፍላጎት በመመሪያ ቁጥር8/2007 መሠረት በህንፃ መዝጋቢ አካል በመመዝገብ በቤት ባለቤቶች ማህበር ይተዳደራል፡፡

## ኣንቀጽ 28. ስለ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ አያያዝና ስለባንክ ሂሳብ አከፋፈት

## 28.1 የኅብረት ሥራ ማህበሩ የገንዘብ አያያዝ

1. ኅብረት ሥራ ማኅበሩ በአቅራቢያ በሚገኝ የ ኢትዮጵያ ንግደ ባንክ ቅርንጫፍ ዝግ የማይንቀሳቀስ የቁጠባ ሂሳብ ወይም የተንቀሳቃሽ ሂሳብ ወይም እንደአስፈላፊነቱ ሁለቱንም ሂሳቦች ይከፍታል፡፡
2. ሂሳቡ በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ስም ሆኖ በማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊመንበር ወይም ሂሰብ ሹም እና በገንዘብ ያዥ ጠሚራ ፊርማ ኃላፊነት ይንቀሳቀሳል፣
3. .በኅብረት ሥራ ማኅበሩ ገንዘብ መያዣ ሳጥን ውስጥ ሊቀመጥ የሚችለው የገንዘብ መጠን ከብር ---------- በላይ መሆን አይችልም፣
4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 ከተጠቀሰው ገንዘብ ውጭ /በስተቀር/ ከአባላትም ሆነ ከሌላ ምንጭ የሚገኝ የማኅበሩ ገንዘብ በ24 ሰዓት ውስጥ ባንክ ገቢ ይሆናል፣

## 28.2 ስለባንክ ሂሳብ አከፋፈት

1) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሁሉም የዳያስፖራ ቤት ልማት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች የሚያገለግል የባንክ ሂሳብ የመክፈት አገልግሎት ብቻ ይሰጣል፣
2) የክልሉ ግብይትና ህብረት ስራ ቢሮ የጋራ አካውንት (pull account) በመክፈት ሁሉም ማኅበራት በእያንዳንዳቸው ሰብሲዲያሪ ሌጅር ተይዞላቸው ከምዝገባው በፊት ወደ ተከፈተው የጋራ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ እንዲያደርጉ ያደርጋል፡፡
3) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ የተደረገውን የእያንዳንዱን ማህበር የገንዘብ መጠን በተመለከተ ማረጋገጫ ለግብይትና ህብረት ስራ ቢሮና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይልካል፣
4) ቤት ፈላጊ የዳያስፖራ አባላት በመመሪያ ቁጥር 08/2007 አንቀጽ 6 ሥር የተገለጹትን ሳይጨምር እንዲገነባላቸው የፈለጉትን የቤት አይነት የክፍያ መጠን በውጭ ምንዛሪ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡
5) ተመዝጋቢዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት ሃገሪቱ በምትገበያይባቸው ገንዘቦች ብቻ ይሆናል፡፡
6) ተመዝጋቢዎች ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዳያስፖራ አካውንት ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፣
7) ነባር ማህበራት ዝግ ሂሳባቸው በሌላ ባንክ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማዞር አዲስ የባንክ ሂሳብ በብር መክፈት ይጠበቅባቸዋል፣



ደ/ብ/ብ/ክ/መ/ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ

## አንቀጽ 29. ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሣብ ምርመራ

1. የግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ በዓመት አንድ ጊዜ የማንኛውንም ኅብረት ሥራ ማኅበር ሂሣብ ራሱ ወይም ቢሮው የሚወክለው ሰው ይመረምራል::
2. የሂሣብ ምርመራ ሪፓርቱም ለጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል::

## አንቀጽ 30 .በኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ሲደርስ ስለሚወሰድ እርምጃ፣

1. የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሣብ ቁጥጥር ወይም ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሥራ እንዲያካሂድ ሃላፊነት የተጣለበት ወይም ተጥሎበት የነበረ ሰው ፣ የማህበሩ ሹም ወይም ሠራተኛ
   1.1. በዚህ አዋጅ፣ በሌሎች በሥራ ላይ ባሉ ሕጎችና በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንቦች ውጭ ያልተፈቀደ ክፍያ ፈፅሞ ከተገኘ፣
   1.2. ዕምነት በመጉደል ወይም ሆን ብሎ በማሰብ ወይም በቸልተኝነት ኅብረት ሥራ ማህበሩ ንብረት ወይም ገንዘብ ላይ ጉድለት አድርሶ ከተገኘ ወይም ለጉዳት ከዳረገ፣
   1.3. የማህበሩ የሆነውን ገንዘብ አለአግባብ ከወሰደ ወይም የሀሰት ማስረጃ ሰነድ ያቀረበ፣ ሰነዶች ያጠፋ፣የሰረዘ፣ወይም ሀሰት የሆነ የምስክር ወረቀት ያዘጋጀ ፣ወይም ፈርሞ የሰጠ፣
   1.4. የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረት ወይም ገንዘብ በማጭበርበር ለራሱ ጥቅም ያዋለ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ እንደሆነ፣

   ተቆጣጣሪው ወይም መርማሪዉ ስለሁኔታው ዝርዝር ማስረጃዎችን በማዘጋጀት ለማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ለአደራጅ መሥሪያ ቤት ሪፓርት ያደርጋል::
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አቀፅ 1 መሠረት ሪፓርት የቀረበለት አደራጅ መሥሪያ ቤት ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በ15 ቀናት ውስጥ መልስ እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል::
3. አጉዳዩ ግለሰብ በተሰጠው ጊዜ ገደብ መልስ ካልሰጠ አደራጅ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን ለፖሊስ ወይም ለአቃቤ ሕግ ወይም እንደሁኔታው ለሁለቱም ያሳውቃል።
4. ይኸው ከተፈፀመ በኋላ ጉድለት አድርሷል የተባለው ሰው ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ያጐደለውን ገንዘብ ወይም ንብረት ከነወለዱ እንዲሁም የሚወሰነውን ካሳና ኪሳራ እንዲመልስ ወይም እንዲከፍል ኅብረት ሥራ ማህበሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥልጣን /ዓደራጅ መ/ቤቱ/ ወይም ዐቃቤ ሕግ ይጠይቃል:: ግለሰቡ ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ወይም አግባብ ያለው ባለሥጣን /አደራጅ መ/ቤቱ ወይም ዐቃቤ ህግ በፍርድ ቤት ክስ በመመሥረት አስፈላጊው ሕጋዊ ርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

## አንቀጽ 31 የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስለሚፈርስበት ሁኔታ

የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩ መፍረስ የሚችለው በኅብረት ሥራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ መስረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፤

## አንቀጽ 32 መረጃ ስለመስጠት፡

የኅብረት ሥራ ማህበሩ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ለግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃዎች የማስተላለፍ ግዴታ አለበት::

## አንቀጽ 33. ስለቅጣት፣

1. አንድ አባል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ጥፋቱ በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠንቶ ለጠቅላላ ጉባዔ ከቀረበ በኋላ ቅጣት ይወሰንበታል፣ የቅጣቱ ደረጃ በውስጠ ደንብ በሚዘረዘረው መሠረት ይሆናል፣
2. በሥራ አመራር ኮሚቴ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ አባል በውሳኔው ካልተስማማ ለሽምግልና ዳኝነት ይቀርባል፣

## አንቀጽ 34 ስለመተዳደሪያ ደንብ ትርጉም

1. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱ አንቀጾች የኅብረት ሥራ አዋጅ መሠረት ይተረጎማል፡፡
2. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች ካሉ በኅብረት ሥራ አዋጅ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
3. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የትርጉም ክርክር የሚያስነሳ ጥያቄ ቢነሳና ስምምነት ላይ ለመድረስ ባይቻል አግባብ ያለው የኅብረት ሥራ ማደራጃ መ/ቤት የሚሰጠው ማብራሪያና ትርጉም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 35 ስለ መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል

1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅት መሻሻል ይችላል፡፡
2. መተዳደሪያ ደንቡ ሊሻሻል የሚችለው ከጠቅላላ አባላት ውስጥ ሁለት ሦስተኛው የሚሆነው እንዲሻሻል ሲወስኑ ይሆናል፡፡
3. በጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ እንዲሻሻል ወይም እንዲቀየር የተደረገ የመተዳደሪያ ደንብ ውሣኔው በተላለፈ 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በሦስት ቅጂ ለክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ መቅረብና መፅደቅ ይኖርበታል፡፡አንድ ተጨማሪ ኮፒ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ገቢ መደረግ አለበት፡፡
4. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበሩ ተደግፎ እንዲሻሻል የቀረበዉ የመተዳደሪያ ደንብ በክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ታይቶ ካልፀደቀ ስራ ላይ መዋል አይችልም፡፡
5. የክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ የቀረበለትን ማሻሻያ ከመረመረ በኋላ ስለማፅደቁ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተም በማሳረፍ አንዱን ቅጂ በመሸኛ ደብዳቤ ለኅብረት ሥራ ማህበሩ መላክ ይኖርበታል፡፡ የፀደቀው መተዳደሪያ ደንብ አንድ ኮፒ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ገቢ መደረግ አለበት፡፡

## አንቀጽ 36 ውስጠ ደንብ ስለማውጣት

የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ መተዳዳሪያ ደንብ ላይ በመመስረት

1. የተለያዩ ዝርዝር ተግባራትን ለመተግበር የሚያስችል ውስጠ ደንብና መመሪያዎችን ማውጣት ይችላል፣ ይህም በጠቅላላ ጉባኤ መፅደቅ አለበት፡፡
2. በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀው ውስጠ ደንብ በክልል ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

## አንቀጽ 37 መተዳዳሪያ ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጸድቆ ለክልሉ ግብይትና ኅብረት ሥራ ቢሮ ቀርቦ ቢሮው ከመዘገበበት ቀን -------------------/200------ ዓም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቅጽ 007

<u>አባሪ አንድ</u>

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወይም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በአፓርትመንት፣ በታውን ሀውስ እና ቪላ በግል የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ የቤት ፍላጎት መግለጫ ቅጽ**

ፎቶ

1. የአመልካች ሁኔታ፣
   1.1. ስም ------------------ የአባት ስም ------------------የአያት ስም ----------------
   ፆታ -------------- ዕድሜ------------------
   ዜግነት---------------------- የፓስፖርት ቁጥር-------------------------------
   1.2 የአመልካች እናት ስም ---------------------- የእናት አባት ስም ------------------------ ----
   የእናት አያት ስም ---------------------------------
   1.3 የመኖሪያ አድራሻ
   - አገር---------------------------------ከተማ-----------------------------
   - ፖ.ሳ.ቁ.------------------------------ ፋክስ ቁጥር-------------------------
   - ስልክ ቁጥር---------------------------ኢ.ሜል -------------------------

   1.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐
   1.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም---------------የአባት ስም---------------- የአያት ስም --------------
   1.6 ተመላሽ ዳያስፖራ ከሆነ ወደ አገር ቤት የተመለሰበት ቀንና ዓመተ ምህረት----------------------
2. የሚፈልጉት የቤት አይነት
   2.1. አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ) ከሆነ ፣
   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

   2.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፣

   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
3. የገቢ ሁኔታ
   3.1. የአመልካች ወርሃዊ የገቢ መጠን በብር -------------------------- ምንጭ -----------------
   3.2. የትዳር ጓደኛ የገቢ መጠን በብር ----------------------- ምንጭ ------------------------------
   3.3. ጠቅላላ የገቢ መጠን በአኃዝ ------------ /በፊደል-----------------------------------
4. የተወካይ መረጃ፤
   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት----------------------------------------------------------

   4.2. የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-
   - ክልል-------------------------ከተማ------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ-----------------------------ወረዳ -------------------------
   - ቀበሌ --------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------
   - የቤት ስልክ ቁጥር -----------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ----------------------
5. ለምዝገባ የሚያስፈልግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ
   5.1 በቅድሚያ በልዩ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጠው ዝቅተኛ መጠን ብር በአኃዝ ------------------
   /በፊደል-------------------------------------------------------------------------------------/
   5.2 የዝግ ሂሳብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ---------------------------------- ቅርንጫፍ ---------------------
6. ሂሳብ የሚከፍትበትና የቤቱን ዋጋ ክፍያ የሚፈጽምበት አማራጭ መንገድ፡-
   6.1. የክፍያ አፈጻጸም በአንድ ጊዜ (100%) ☐ በሁለት ጊዜ (50%) ☐
7. እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

7.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኔን፣
7.2 በኢትዮጵያ ውስጥ በየትኛውም ከተማ በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በመንግስት በተዘረጉት የቤት ልማት ፕሮግራሞች ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኔን፣
7.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ማስቀመጤን፣ ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊትገቢ የማደርግመሆኔን፣
7.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣
7.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረክብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኔን፣
7.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም
7.7 ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም-------------------------- ፊርማ ------------------------------- ቀን -----------------------

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ በግል ተመዝጋቢዎች ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡

ቅጽ 005

<u>አባሪ ሁለት</u>

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ**

1. የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ----------------------------------------------------------------የመኖሪያቤት የህ/ስ/ማ
2. የአመልካች ሁኔታ፣

   2.1. ስም --------------- የአባት ስም ----------------የአያት ስም --------------------
   ፆታ -------- ዕድሜ------------ ዜግነት--------------- የፓስፖርት ቁጥር------------

   ፎቶ

   2.2 የአመልካች እናት ስም ----------------------- የእናት አባት ስም ---------------------------
   የእናት አያት ስም-------------------------------------

   2.3. የመኖሪያ አድራሻ
   2.3.1 አገር-------------------------------------
   2.3.2 ከተማ-------------------------------------

   2.4 የትዳር ሁኔታ
   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

   2.5. ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም ----------------የአባት ስም-----------------የአያት ስም--------------

   2.6. ተመላሽ ዳያስፖራ ከሆነ ወደ አገር ቤት የተመለሰበት ቀንና ዓመት ምህረት-----------------------
3. የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት

   3.1 አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ) ከሆነ፣
   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

   3.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፣
   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐
4. የተወካይ መረጃ፣

   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት--------------------------------------------------------------------

   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ :-
   - ክልል---------------------------ከተማ--------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ---------------------------------ወረዳ ---------------------------
   - ቀበሌ ----------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------
   - የቤት ስልክ ቁጥር ------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር -----------------------

5 እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

5.1 ቀደም ሲል በመንግስት በተዘረጉት በማናቸውም የቤት ልማት ፕሮግራሞች ያልተመዘገብኩ መሆኔን፣

5.2 በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በማናቸውም ከተሞች በራሴ ወይም በትዳር ጓደኛዬ ስም የተመዘገበ የመኖሪያ ቤት ወይም የቤት መስሪያ ቦታ የሌለኝ እና ከዚህ በፊትም የነበረኝን በሽያጭ ወይም በስጦታ ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፍኩ እና በቤት ልማት ፕሮግራም ከዚህ በፊት ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኔን፣

5.3 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 50 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ እና ቀሪውን 50 በመቶ መሬት ተዘጋጅቶ የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት ገቢ የማደርግ መሆኔን፣

5.4 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.5 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የተስማማሁ መሆኔን፣

5.6 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

5.7 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያሟላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-----------------------------------

ፊርማ ------------------------------

ቀን ---------------------------------

ማሳሰቢያ፡- ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህብረት ሥራ ማህበሩ አባል ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡